# የገለልተኛ (የግል) ተቋራጭ ጥበቃዎች ድንጋጌ የእውነታ ወረቀት

የዚህ ሰነድ የተተረጎመ እትም ሲጠየቅ በ (206) 256-5297 ይገኛል።



የሲያትል የገለልተኛ (የግል) ተቋራጭ ጥበቃዎች ድንጋጌ ውል ከመግባቱ በፊት <u>እና</u> ክፍያ በሚፈፀምበት ጊዜ በድንጋጌው የተሸፈኑ የቅጥር አካላት ለገለልተኛ ተቋራጮች መግለጫዎች እንዲያቀርቡ ያስፈልጋል። ገለልተኛ (የግል) ተቋራጮች ማካካሻው በሚከፈልበ ቀን ወይም ከዚያ በፊት መከፈል አለባቸው ይኸዉም  በውሉ ስምምነቶች መሠረት፣ በቅድመ ውል የተገለጹ ነጥቦች፣ ወይም በ30 ቀናት ውስጥ። ይህ ህግ **ከመስከረም 1፣ ቀን** 2022 **ጀምሮ** ተግባራዊ ይሆናል።

## ሽፋን

**በዚህ ህግ የሚሸፈኑት ሰራተኞች የትኞቹ ናቸው?**

ገለልተኛ ሥራ ተቋራጭ ማለት አገልግሎቶችን ለመስጠት እና ክፍያ ለማግኘት በአንድ የቅጥር ተቋም ተቀጥሮ በግል የሚተዳደር (self-employed) ሰው ነው። ይህ ህግ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ከጥቂቶች በስተቀር[1] ሁሉንም የገለልተኛ ስራ ተቋራጮችን ይመለከታል።

**በዚህ ህግ የተሸፈኑት የትኞቹ ኩባንያዎች ናቸው?**

ይህ ህግ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ንግዶችን ጨምሮ በመደበኛነት በንግድና ወይም በንግዳዊ እንቅስቃሴ ላይ የተሰማሩ ቀጣሪ አካላትን ይመለከታል።

**በዚህ ህግ የተሸፈኑት ኮንትራቶች የትኞቹ ናቸው?**

ይህ ህግ በአገልግሎታቸው ባህሪ እና በአገልግሎታቸው ዋጋ ላይ የተመሰረተ ውሎችን ይሸፍናል።




---

[1] በዚህ ህግ ያልተሸፈኑ ገለልተኛ ተቋራጮች ጠበቆች፣ ከቀጣሪ አካል ጋር ያለው የአንድ ገለልተኛ ስራ ተቋራጭ ግንኙነት ሁኔታዎች በንብረት ኪራይ ውል ብቻ የተገደበ (ለምሳሌ በሳሎን ውስጥ ዳስ የሚከራይ ፀጉር አስተካካይ) እና በስራ ደረጃዎች ጽህፈት ቤት የዳይሬክተር ደንብ በተገለጸው መሰረት ሌሎች ገለልተኛ ስራ ተቋራጮች ናቸው። ደንብ የማውጣት ሂደቱ በ2022 መጀመሪያ/አጋማሽ ላይ እንደሚሆን ይጠበቃል። ለ [የሥራ ደረጃዎች ጽህፈት ቤት (OLS) ጋዜጣ] ይመዝገቡ ወይም ለዝማኔዎች የሥራ ደረጃዎች ጽህፈት ቤት ድህረ ገጽን በ: www.seattle.gov/laborstandards ይመልከቱ።

የሲያትል የሥራ ደረጃዎች ጽህፈት ቤት

*ይህ ሰነድ የሕጉን ማብራሪያ ይሰጣል። <u>ማስታወሻ</u>: በሥራ ደረጃዎች ጽህፈት ቤት የቀረበው መረጃ እንደ ሕጋዊ ምክር፣ የተወካይ ድርጅት ውሳኔ ለመፍጠር፣ ወይም ከአንባቢው ጋር የጠበቃ ደንበኛ መብትን ለማቋቋም አያገለግልም። ይህ ለሕጎች እና ደንቦች ምትክ ሆኖ መጠቀም የለበትም።*

Seattle Office of Labor Standards

### መሟላት የሚያስፈልጉ
## የወቅታዊ ክፍያ መስፈርቶች

ቀጣሪ አካላት “ወቅታዊ ክፍያ” ለገለልተኛ ተቋራጭ መስጠት ያለባቸው:

1) የኮንትራቱ ውሎች፤
2) የቅድመ-ውል ስምምነቶች መገለጥ፤ ወይም
3) በ 30 ቀናት ውስጥ።

## የተደነገገዉን ደንብ ይፋ ማድረግ

ቀጣሪ አካላት የሚከተሉትን የቅድመ-ውል እና የክፍያ ጊዜ መግለጫዎችን ለሁሉም ሽፋን ያላቸው ገለልተኛ ሥራ ተቋራጮች መስጠት አለባቸው፣ ከማመላለሻ አውታረ መረብ ኩባንያ አሽከርካሪዎች ***በስተቀር*** (ለምሳሌ የኡብር (Uber) እና ሊፍት (Lyft) ሾፌሮች)። በሚቀጥሉት ወራት፣ የሥራ ደረጃዎች ጽህፈት ቤት የቅጥር አካላት ይህንን መረጃ ለማቅረብ ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸውን አብነቶች ይለቃል- ለዝማኔዎች ድረ-ገጻችንን እዚህ ይመልከቱ።

### 1. ቅድመ-ውል የይፋ ማድረግ አስፈላጊነቶች

| | |
|---|---|
| ▪ *ቀን* | ▪ *የክፍያ መሠረት* |
| ▪ *የገለልተኛ ተቋራጭ ስም* | ▪ *ጠቃሚ ምክሮች እና/ወይም የአገልግሎት ክፍያ ስርጭት ፖሊሲ* |
| ▪ *የቅጥር አካል ስም + የእውቂያ መረጃ* | ▪ *የሥራ ወጪዎች ሆነው በቀጣሪ አካል የሚከፈሉ ወጪዎች* |
| ▪ *የሥራው መግለጫ* | ▪ *ተቀናሾች፣ ክፍያዎች ወይም ዋጋዎች* |
| ▪ *የሥራ ቦታ* | ▪ *የክፍያ መርሐግብር* |
| ▪ *የክፍያ መጠን ወይም የክፍያ ተመኖች* | |

### 2. የክፍያ ጊዜ መግለጫዎች ተፈላጊነት

| | |
|---|---|
| ▪ *ቀን* | ▪ *ጉርሻዎች፣ ማካካሻ እና/ወይም የአገልግሎት ክፍያ ስርጭት* |
| ▪ *የገለልተኛ ተቋራጭ ስም* | ▪ *የክፍያ መሠረት* |
| ▪ *የቀጣሪ አካል ስም* | ▪ *ከቀጣሪ አካል ተመላሽ የሚሆን ወጪ* |
| ▪ *በክፍያ የተሸፈኑ አገልግሎቶች መግለጫ* | ▪ *ጠቅላላ ክፍያ* |
| ▪ *በክፍያ የተሸፈኑ አገልግሎቶች ቦታ* | ▪ *ተቀናሾች* |
| ▪ *የክፍያ መጠን ወይም የክፍያ ተመኖች* | ▪ *ከተቀናሾች በኋላ የተጣራ ክፍያ* |

## የሲያትል የሥራ ደረጃዎች ጽህፈት ቤት

የእኛ ተልዕኮ በነቃ ማኅበረሰብና በንግድ ሥራ ተሳትፎ፣ በስልታዊ አፈጻጸም እና የፈጠራ ፖሊሲ እድገት፣ ከዘርና ከማህበራዊ ፍትህ ቁርጠኛ አቋም ጋር የስራ ደረጃዎችን ወደፊት ማራመድ ነው።

**የእኛ አገልግሎቶች**
ቅሬታዎችን መመርመር
ሠራተኞችን ባሉበት መድረስ
የቴክኒክ ድጋፍ ለንግድ ሥራ
ግብዓቶችና የማስተላለፍ ሥራዎች

ቋንቋ የማስተርጎምና የጽሑፍ ትርጉም አገልግሎት ማግኘት አለ። የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች ተገቢነት ያለው መስተንግዶዎች (ኣገልግሎቶች) ይሰጣል። አገልግሎቶች ነፃ ናቸው።

**ተጨማሪ መረጃ**
(206) 256-5297 ይደውሉ:
ኢሜይል :
labourstandards@seattle.gov
seattle.gov/laborstandards ይጎብኙ:

### መርጃዎች/ ምንጮች

**ለቀጣይ ዝመናዎች፣ ድህረ ገጻችንን ይጎብኙ ወይም ለጋዜጣችን በ www.seattle.gov/laborstandards ይመዝገቡ ።**
ስለ ገለልተኛ ተቋራጭ ጥበቃዎች ድንጋጌ የበለጠ ያንብቡ፣ እዚህ
http://www.seattle.gov/laborstandards/ordinances/independent-contractor-protections-

የሲያትል የሥራ ደረጃዎች ጽህፈት ቤት
*ይህ ሰነድ የሕጉን ማብራሪያ ይሰጣል። ማስታወሻ: በሥራ ደረጃዎች ጽህፈት ቤት የቀረበው መረጃ እንደ ሕጋዊ ምክር፣ የተወካይ ድርጅት ውሳኔ ለመፍጠር፣ ወይም ከአንባቢው ጋር የጠበቃ ደንበኛ መብትን ለማቋቋም አያገለግልም። ይህ ለሕጎች እና ደንቦች ምትክ ሆኖ መጠቀም የለበትም።*